# በቤኒሻንጉል ክልል በሕዝብ ማመላለሻ ላይ በተፈጸመ ጥቃት ቢያንስ 20 ሰዎች ተገደሉ

4 መጋቢት 2022




**በምዕራብ ኢትዮጵያ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ታጣቂዎች በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ላይ ጥቃት ፈጽመው ቢያንስ 20 ሰዎች መግደላቸውን አንድ የክልሉ ኃላፊ ለቢቢሲ ተናገሩ።**

ጥቃቱ ስለመፈጸሙ የሚያውቁና ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ እኚህ የቤኒሻንጉል ክልል ከፍተኛ ኃላፊ ለቢቢሲ እንደተናገሩት ከመተከል ወደ ጉባ በመጓዝ ላይ በነበረ አውቶብስ ላይ ረቡዕ የካቲት 23/2014 ዓ.ም. ጥቃት መፈጸሙን

አረጋግጠዋል።

አፍሪካ እርሻ ልማት በሚባለው አካባቢ ላይ ያደፈጡ ታጣቂዎች በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ላይ በፈጸሙት ጥቃት ለጊዜው ትክክለኛው ቁጥር ባይታወቅም ከ20 በላይ የሚሆኑ ሰዎች ህይወት ጠፍቷል።

ቢቢሲ ከክልሉ የፀጥታ አካላት ስለጥቃቱ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ተደጋጋሚ ጥረት ያደረገ ቢሆንም ለጊዜው ምላሽ አላገኘም።

ኃላፊው እንዳሉት ጥቃቱ የተፈጸመው ከሱዳን በኩል ሰርገው በሚገቡ 'ፀረ ሰላም ኃይሎች' መሆኑን አመልክተው፣ ታጣቂዎቹ ከዚህ በፊትም ተመሳሳይ ጥቃቶችን በሰላማዊ ሰዎች ላይ ይፈጽሙ እንደነበር አስታውሰዋል።

- ያልተሰማው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ድምጽ እና መፍትሄው
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ያለው አለመረጋጋት፣ የሰላም ጥረትና ፈተናዎቹ
- 4ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ አረፉ

ከጥቂት ወራት ወዲህ ክልሉ ከፌደራል መንግሥት ጋር በመቀናጀት በወሰደው መረጋጋት የማስፍን እርምጃ በአካባቢው በታጣቂዎች ሲፈጸም የቆየውን ጥቃት መቆጣጠር ተችሎ የነበረ መሆኑንም ኃላፊው ጠቅሰው የአሁኑ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የመጀመሪያው ነው ብለዋል።

በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን በሚመለከትም ከመተከል ወደ ጉባ የሚሄዱ የተለያዩ የኅበረተሰብ ክፍል አባላት መሆናቸውን እንጂ ስለማንነታቸው እስካሁን በዝርዝር የታወቀ ነገር የለም።

ጥቃቱን ተከትሎም የክልሉ ፀጥታ ኃይል ፈጻሚዎቹን ለመቆጣጠር እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ኃለፊው ለቢቢሲ ተናግረዋል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምዕራብ ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር የሚወሰን ሲሆን፣ በቅርቡ የኤልክትሪክ ኃይል ማመንጨት የጀመረው ግዙፉ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ይገኝበታል።

ባለፉት ተከታታይ ዓመታት በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች በሰላማዊ ሰዎች ላይ ተደጋጋሚ ጥቃትን በመፈጸም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን የገደሉ ሲሆን በርካታ ሺዎች ደግሞ ከቀያቸው እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆነዋል።

ታጣቂዎች በሚፈጽሙት አሰቃቂ ጥቃቶች የተነሳ ከሁለት ዓመት ወዲህ አብዛኛው የክልሉ ክፍል በቤኒሻንጉል ክልል እና በፌደራል መንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በሚመራ የዕዝ ማዕከል [ኮማንድ ፖስት] ስር ሆነው ቆይተዋል።

የቤንሻንጉል ክልሉ ካማሺ፣ መተከል እና አሶሳ በሚሰኙ ሶስት ዞኖች የተዋቀረ ነው።